ገንቱ ውእቱ ትእምርተ ሰላም፤

ዘረሰዮሙ አሐደ ለክልኤሆሙ ፤ ኤፌ ምዕ ፪ ቍ ፲፬

፲፰ኛ ዓመት ቍጥር ፬

አ ፡ አ ፡ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ. ም.

# ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ይህ ድርሰት ለሃይማኖትና ለምግባር ለጊዜውም ዜና መዋዕል መግለጫ የንባቡን ቀጥተኛ ትርጉሜ ከመከተል ጋር ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ መታሰቢያ ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ተሰየመ ።

በወር ሁለት ጊዜ ይወጣል ።
የስልክ ቍጥር 13000/4
የፖስታ ሳጥን ቍጥር 12.83

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክና ዜና ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት ታተመ ።

የድርሰቱ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 1.20
» » አንዱ 0.5
ለውጭ አገር እጥፍ ይሆናል ።

## የጻድቅ ሰው መታሰቢያ

### ለዘለዓለም ጻድቅ ይኖራል ። መዝ ፻፲፩ ፥ ፮

ከመልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ።

በኢትዮጵያችን በጣም ከፍ ከፍ ያሉ ጻድቃን በየጊዜው እየተነሡ የክርስትና ሃይማኖት እንዲስፋፋ ፤ እምልክተ ጣዖት እንዲጠፋ ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ መካከል የክርስትና ደሴት ሁና እንድትኖር አድርገዋል የነዚህም ጻድቃን ቁጥር እንደባሕር አሸዋ ፤ እንደ ሰማይ ከከብ የበዛ በመሆኑ አሁን በዚህ ትንሽ ጋዜጣ ዓምዳችን ለመግለጥ እጅግ አድካሚ ይሆናል። ይሁን እንጂ ከነዚህ ሁሉ ጻድቃን



ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ስለ ሀገራቸው በአንድ እግራቸው ቁመው ሲጸልዩ።

መካከል የቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ስም እጅግ ደምቆና አሸብርቆ ይታያል ።

ይህ የሆነበት ምክንያት በጣም ግልጥ ነው ። ፩ኛ. አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት እንደሌሎች መናንያን በበታ በመወሰን ጊዜያቸውን አላሳለፉም ግን ከበታ ወደ በታ ከሀገር ወደሀገር በመዘዋወር ወንጌልን በሰፊው አስተምረዋል ። ጥቂትም ቆየት ብለው የአገዘሩውን ስፋት ፤ የሠራተኞቹን ማነስ ተመልክተው ፲፪ ቱን ንቡራነዕድ ሹመው በየክፍለ ሀገራቸው እየተዘዋወሩ እንዲያስተምሩ ማድረጋቸው እጅግ ከፍ ያለ ዘዴ ስለነበር በበለጠ በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቁ አድርጎቸዋል ።

፪ተኛ. በመንፈሳዊ ሥራ ብቻ ሳይወሰኑ በማኅበራዊውም ኑሮ በኩል ከፍ ያለ አስተያየት ስለነበራቸው በመከፍ ያለ አስተያየት ... በመግባት ከፍ ያለ ሥራ በመሥራታቸው ንጉሡ አፄ ይኩኖ አምላክ በጣም ተደስተው ለቤተ ክርስቲያን ሢሶ መንግሥት ሲሰጡ የዚህ አስተዳዳሪ መሪው አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንዲሆኑ መርጠው እጨጌ የሚለውን ሙዓርግ ሰጥተዋቸዋል ። ከዚያም ወዲህ ደብረ ሊባኖስ የአባታችን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም በእጨጌዎች የሚተዳደር ሁኗል ።

፫ተኛ. የኢትዮጵያ ብርሃን የነበሩት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ግብፅንና ኢየሩሳሌምን ጐብኝተው በግብፅ አገር በሚገኙት ታላላቅ ገዳማት ብዙ ጊዜ አሳልፈው መጻሕፍትንም ተመራምረው ቢመለከቱት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከጽጽስና መዓርግ የተከለከሉት ያለ አግባብ መሆኑን ተረድተው ወደ እግዚአብሔር ቢጠይቁ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦላቸው የጽጽስና መዓርግን ገንዘብ አድርገው በኢትዮጵያ መሬት ቅስናና ዲቁና እየሰጡ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲከፈቱ ሊቃውንት እንዲበረክቱ በማድረጋቸው ከዚያ ወዲህ ብዙ ድክም ፈጥሮ የነበረውን ከባድ ቀንበር ገና በ፲፫ተኛው መቶ ዘመን ሰብረው ጥለውት እንደነበረ ስናስታውስ እንኳንስ በዘመናቸው ለነበረው ሕዝብ እኛንም ከፍ ወደ አለ አድናቆት ያደርሰናል ።

ይሁን እንጂ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ራሳቸውን በጾም በጸሎት ፤ በአገልግሎትና በትህርምት ወስነው ሲኖሩ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ እየተገለጠ ብዙ ተአምራት አሳይቷቸዋል። ይኸውም ተብሎ ዘሎ ስለ ተነገረ ተወዳጁ ሰት የራቀ ፤ እውነትን የተመረኮዘ በመሆኑ እነሆ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያን በስብከተ ወንጌላቸው የሚያበሩልን የአባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ልጆች ናቸው ።

ዓላማቸው ተፈጽሞ በንቡራነ እዶቹ ምትክ በሀገሯ ሊቃነ ጳጳሳት በኢትዮጵያ ተበትነው ሲያስተምሩ፤ ሲመክሩ ስናይ ደግሞም በአባታችን ተወጥኖ የነበረው የጽጽስና መዓርግ በተወላጆቹ እየሰጡ ሲገኝ አድናቆታችን እየበዛና እየበረከተ ይሄዳል ።

አሁንም ቢሆን ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት በሀጸደ ነፍስ ሁነው ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ጸሎታቸውን በለማኟረጥ ወደ ፈጣሪያቸው ያቀርባሉ ።

በዚህ በታ ተሰብስበን መታሰቢያቸውን በምናከብርበት ቀን ከኛ ጋራ በረድኤት አሉ ። በጸሎታቸው ይረዱናል ይደግፉናል። ሁላችንም የአባታችንን ምሳሌ እንከተል ። መላ ሕይወታቸውን የጸሎትን ሃይማኖታችንን እናጽና ።

www.ethiopianorthodox.org

# ስለ ልደት በዓል ።

አከባበር በቅዱስ ሲኖዶስ ተጠ ንቶ ለምእመናን የተሰጠው ውሳኔ ባለፈው ዜና ቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ነበር ግን ጠያቂዎቻችን ስለ በዙ ሁለተኛ ታትሞ ያልደረሳቸው እን ዲደርሳቸው አድርገናል ።

## ውሳኔውም ይህ ነው ።

አበ ባስልዮስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ

## ተክለ ሃይማኖት ።

በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. በዘመነ ዮሐንስ ልደት ዓርብ ውሎ ስለነበረ ፣ ጉዳዩ በሲኖ ዶስ ታይቶ በፍትሐ ነገሥት ሥርዋጽ ፤ ገቢረ በዓልሰ አኮ በመብልዕ ፤ በዓል የሚከበረው በመብል ብቻ አይደለም ስለሚልና ገሃድም ያልተጸመለት ዓርብና ረቡዕ የቅባት ምግብ መብላት ስለማይገ ባው ልደት ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ሐሙስ በቅ ባት ምግብ እንዲከበር ፤ ጥንተ ልደቱ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ዓርብ በማግሥቱ በጾም ፤በጸሎት ፤ በዝማሬ፤ በማኅሌት ፤በቅ ዳሴ እንዲከበር ተወስኖ ተከብሯል ።

አሁን ደግሞ በ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. ዘመነ ዮሐንስ በሆነበት ዘመን ጥንተ ልደቱ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ረቡዕ ስለሆነ ስለዚሁ ጉዳይ ዛሬም በሊቃነ ጳጳሳቱና ኤጲስ ቆጶሳቱ ሲኖዶስ ታይቶ ልደት ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ማክሰኞ ሌሊት በስብሐተ እግ ዚአብሔር ፤ በዝማሬ፤ በማኅሌት ቅዳሴው ም በሌሊት ተፈጽሞ በዓለ ልደቱ በሥጋ በቅባት ምግብ በተድላ በደስታ ተከ ብሮ እንዲውል ፤ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ረቡዕ ጥንተ ልደቱ የዋለበት ቀን ስለሆነ እን ደ መጽሐፉ ሥርዓት ጾሙ ሳይሻር በዝ ማሬ ፤ በማኅሌት ፤ በቅዳሴ ተከብሮ እንደተ ለመደው ቅዳሴው ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት እንዲፈጸም ።

ስለልደትና ጥምቀት ሰኞ በሚውል በት ዘመንም ቅዳሜና እሁድ ገሃድ ነው በማለት ስለሚያከራክር ሁለት ገሃድ ስለ ሌለ ልደት ፤ጥምቀት ሰኞ በሚውል በት ዘመን ገሃድ አንድ ቀን እሑድ ብቻ ከቅባት ምግብ መባልዕት ተከልክሎ በጾም እንዲከበር ተወስኗል ።

ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤዎችም ላይ የቤተ ክርስቲያናቸው ወኪል በመሆን ብዙ ጊዜ ተገኝተዋል ።

አቡነ ፓላዲያን ትልቅ ደራሲ ነበሩ ሠላሳ ያህል መጻሕፍት ደርሰው አሳት

ተከታዩን በ፬ኛው ገጽ ይመልከቱ ።

# አምስተኛ

## የወንጌል መልእክተኞች ጉዞ ።

የወንጌል መልእክተኞቹ ፲፱ ቀን ከሰዓት በኋላ ተነሥተው ጉዞአቸውን ከደብረ ሲና ወደ አርማንያ ቀጠሉ በዚሁም ቦታ ማለት ማፋድ ወረዳ ግዛት አርማንያ ከተማ እንደደረሱ ከወረዳው ገዥ ከግራዝማች ድምሩ ደምሴ ከወረ ዳው ፖሊስ አዛዥ የመቶ አለቃ ተፈራ ለማ እንዲሁ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር ተገናኝተው ስለ ማኅበሩ ዓላማ በሰፊው ከተናገሩ በኋላ እንዲህ ያለውን ቅዱስ ዓላማ ይዋል ፤ ይደር ተብሎ ቀጠሮ ሊሰ ጠው አይገባውም ብለው ሕዝቡን ሰብ ስበው በመመከከር ከአሥር ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ ተነጋ ግረው ወዲያውኑ ምርጫውን ቀጥለው ከፕሬዚዳንት እስከ አባሎች ድረስ መር ጠው ፈጽመው አቋቁመዋል ።

ኅዳር ፳ ቀን ፶፮ ዓ ም የአርማ ንያ ሕዝብ የወንጌል መልእክተኞቹን ጠርቶ ዛሬ ከእኛ ጋር ዋሉልን ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን አክብሩልን ብሎ ስለጠ የቃቸው መልእክተኞቹ የሕዝቡን ሐሳብ ተቀብለው ኅዳር ጽዮንን ከዚያ አክብ ረው እንዲውሉ ፈቀዱ ፤ ቢሆንም ሙሉ ቀን ሥራ ፈቶ መዋል ስላልተቻለ መል እክተኞቹ ማታ እንመለሳለን ብለው ጉዞአቸውን ወደ ሮቢት ከተማ ቀጥ ለው ሮቢት ከተማ እንደደረሱ በከተ ማው ጭቃ ሹም በአቶ ተሰፋዬ ሀብተ ሚካኤል አማካይነት ከፊታውራሪ ተሰማ እርገጤና ከአጥቢያ ዳኛው ከባሻ ጌታ ነህ ዘውዴ እንዲሁም ከኮሎኔል መኰ ንን ወርቄና ከቀኛዝማች መሐመድ አሉ ጋር ተገናኝተው ከተነጋገሩ በኋላ በጠ ቅላላ ባለሥልጣኖችና የአገሩ ሽማግሌ ዎች የከተማው ሕዝብ ተሰበሰበ፤ መልእ ክተኞቹም ለተሰበሰበው ሕዝብ ስለማኅ በሩ ዓላማ ሰፊ ንግግር ከደረጉ በኋላ ሕዝቡ ተሰብስቦ በደስታ ምርጫውን ቀጠለ። ምርጫውንም ከፕሬዚዳንት እስከ አባሎች ድረስ መርጠዋል ፤ ከሽማግሌ ዎቹም እየተነሡ እንዲህ ያለው ማኅ በር በየትም ቦታ እንዲቋቋም ተገቢ ነው ፤

# ጸሎተ ፍትሐት ።

ስለ ብፁዕ አቡነ ፓላዲያን ዕረፍት ጥቅምት ፬ ቀን ፶፮ ዓ. ም. ብፁዓን ጳጳሳት ፤ ክቡራን ሚኒስትሮች ፣ ኮር ዲፕ ሎማቲክችና ብዙዎች ታላላቅ ሰዎች የቅድስት ሥላሴ መ| ኮሌጅ መምህራንና ተማሪዎች በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት ተደ ርሶላቸዋል ።

በጸሎተ ፍትሐቱም ላይ ከመ| ኮሌጅ ተማሪዎች አንዱ አቶ አዕምሮ ወንድም አገኘሁ ከዚህ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

ብፁዓን አባቶቻችን ክቡራን ፤ ሚኒስ ትሮች ፤ እንዲሁም የተከበራችሁ እንግዶ ቻችን ።

ዛሬ ስለ ብፁዕ አቡነ ፓላዲያን እረፍት በምናደርገው ጸሎተ ፍትሐት ላይ ይህን አጭር ንግግር በእኔና በጓደኞቼ ስም እንዳደርግ ዕድል በማግኘቴ ኃዘንም ደስታም ይሰማኛል ።

ብፁዕ አቡነ ፓላዲያን እንደ አ. አ. በ፲፱፻፲፬ ዓ. ም· በሶርያ ውስጥ ቂሳብ በምትባል ቀበሌ ተወለዱ ። በዘር ያር መን ተወላጅ ሲሆኑ ፣ በዜግነታቸው ሊባኖሳዊ ነበሩ ። ለትምህርት ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ በልዩ ልዩ የአርመን ሲምናር ችና ኮሌጆች ገብተው ሥጋዊና መንፈ ሳዊ ትምህርቶችን አስተባብረው ተማሩ ። ከዚያም ወደ አሜሪካን ሀገር ሔደው በልዩ ልዩ ትምህርቶች ልዩ ልዩ ከፍ ተኛ ዲግሪዎችን አገኙ ። እንደ አ. አ. በ፲፱፻፵፬ ዓ, ም. በኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ በመንፈሳዊ ትምህርት የዶክ ተርነት ዲግሪ ተቀበሉ ፤ በዚህ አኳኋን በበለጠ የመንፈሳዊ ትምህርት ዕውቀት ዘርፎችን መገብየት በማሰብ ብዙ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ፣ ትምህርታቸ ውን እንዳጠናቀቁ ወደ ተወለዱበት ክፍለ ሀገር ተመልሰው አስተማሪ በመሆን ሠሩ ። ቀጥሎም በቤይሩት ያንድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት| ቤት (ሲሚናር) ዲን ሁነው አሥራ ሁለት ዓመት አገለገሉ ። በእን ዲህ ያለም ሥራ ላይ ሳሉ በተወለዱ በ፴፫ ዓመታቸው የጵጵስና ማዕርግ ተቀ ብለው ቤተ ክርስቲያናቸውን በሚመለ ከቱ ጉዳዮች ሁሉ ከፍ ያለ የሥራ ፍሬ አሳይተዋል ። ይልቁንም በልዩ ልዩ ክፍለ ዓለም የሚኖሩትን አርመናውያን ክርስቲያኖች ዙረው በመጐብኘትና በማ ስተማር የሚፈለግባቸውን የጠባቂነት አገልግሎት ፈጽመዋል። በዓለም አብያተ

www.ethiopianorthodox.org

ተለይም ለኛ ይጠቅመናል ብለን እና
ናለን ብለው ተናግረዋል ።

ከዚህ በኋላ የወንጌል መልእክተ
ቹ በተቃጠሩት መሠረት ከሮቢት ከተማ
ደ ጉጅ አምባ ማርያም ቀጥለው ኅዳር
፩ ቀን ፶፯ ዓ ም ከንጋቱ በ፲ ሰዓት
ቀደም ብለው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ
ሪደው ሥራቸውን ቀጠሉ ከህናቱ ቅዳሴ
እስኪ ገቡ ድረስ ለተሰበሰበው ሕዝብ
ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተዋል ጸሎተ
ቅዳሴውም ከተፈጸመ በኋላ ታቦቱ ወጥቶ
ከመግባቱ በፊት ሰፋ ያለ ትምህርት
ማለት ስለታቦተ ጽዮን ንግግር አድር
ገዋል ከዚህ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ሁኗል ።

# ስለ ስብከት
## ጾምና ስለ ብሥራት ።

ከይቁም ግዛው ።

ስለጽድቅ ብለው የሚርቡቸው
ንዑዳን ክቡራን ብፁዓን ናቸው ፤
ዓርብ ረቡን ሥጋ ቢቀር በተሻለ
የጾም ምግብ አትክልት ለለት ያህል ከለ
(ያ እህል ከለ) ።
እንኳን ሌሊትና ቢሰብክ ቀንም
በስብከት አይቀርም የምእመናን ጾም
ስቡን ሥጋ ከትተው ሲበሉ በጾም
እናት ኢትዮጵያ ስብ ከታ አትበላም ።
አንዳንዶችም አሉ አፍረው የሚበሉ
ፊታቸውን በልብስ ሸፍንፍን እያሉ ።

እንዳይሳሣቱ ልጆቼ ሲማሩ
ጠቅል የኛ መምህር ኃ ያሉ ይንገሩ ።

ሀ ለ ሐ ሳይጠፋኝ ቀጥሎ ታጣኝ
መ ብል ይሻል ይሆን እስቲ ንገሩኝ ?

ከጾ ተነሥቼ በጽ ጨረስኩ ያልኩት
ገና ጾም ኖረሎይ መጨረሻው
ትምህርት ።

ጽንቱን አውቀዋል ሳድሱን ሲቈጥሩ
ጾም እንዳይቀርብን ሳብዑን ያስተምሩ ።
ሰወቹም ይላሉ መብል ምንአለበት

አዳም በመብል ነው ያገኘው የሞት ሞት ፤
የረቀቀ ሲሆን የፈጣሪ ምሥጢር
ከማድነቅ በስተቀር መመራመር ይቅር ።

ዳቦ ብቻ ነወይ የጾሙ ግብግሆ
ምነው አትሰጠን በጾም ከጠላህ ።

የቅዱሳን ምግብ የጻድቃን ሲሳይ
ገዳማቱ ሁሉ ጠል አይደለም ወይ ።

ለቤተ ክርስቲያን ብሰግድ ብጾም
እረከ ነበረ ጠላተ ገዳም ።

ከጠላው ታግሼ በሰው ጥዬ አሳቤን
ማር ብዬ በለመንኩ የሚጣፍጠውን
ማርና ክርስቶስ ይላል መሀይምን
አምላክ ፈጣሪውን አዝኖ ሲለምን ።

ማርና ክርስቶስ ለምሳሌነቱ
አውራው ድምፅ መልአክ ዕጩ የዕንሰቱ
ማሩ የማርያም ንቡ የልደቱ ።

# ም ክ ር ።

ከለፈው ተሃይማኖት ጋዜጣ የቀጠለ
ከአባ ተድላ ገብረ ዮሐ ንስ።

ብንበላ ምነው እንደልማዳችን ፤
ስለምን ይቀራል የቀድሞ ባህላችን ፤
በአንድነት እንኑር እንዳባቶቻችን ፤
እንዳይረሳብን ያለፈው ቅርሳችን ።
ሸፍን ምግብ አሉት እንደልማዳቸው ፤
እውነተኛው ጻኛ አያይም መስሏቸው ።
ለጤንነት ነበር ምግቡ የተሠራ ፤
የሆድ ሕመም ሆነ ሆነን ባላጋራ ፤
ጤና የፈለገ ያምላክን ሕግ ይሥራ ።
እኔ ልንገራችሁ ደግሜ ደግሜ ።
ጾምን ላከበረ ይሰጠዋል ዕድሜ ፤ .
ለሥጋ አትሣሱ ስሙኝ የምክር ቃል ፤
ለሥጋው ያደላ ማዕረጉን ይጥላል ።
የዘመኑ ልጆች ከአባት ተገኝታችሁ ፤
አባት መበደልን ለምን ተማራችሁ ?
ርስቱና ጉልቱን ገንዘቡን ወዳችሁ ፤
ለአባት መታዘዝን ስለምን ጠላችሁ ?
አባትን አክብሩ እኔ ልምከራችሁ ።
እንዲሆን የጸና የኋላው ቤታችሁ ።
ዘመኑ ክፉ ነው ለምን ትላላችሁ ?
እናንተ ራሳችሁ እየበደላችሁ ፤
የጥበብ መቅድሙ አምላክን መፍራት ነው
ይኸን ያልተማረ ጥበቡ ከንቱ ነው ።
ራበን ቸገረን ለምን ትላላችሁ ?
አምላክ ይሰጠናል ጥጋብ ከቻላችሁ ።

# ራስ ዳሽን በሰሜን

ከአለፈው ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣ የቀጥር ፯ ተከታይ ።

ቅዱስ ያሬድ የጸለየበትን ተራራ
ብጭሩ ገልጸናል በዚሁ ተራራ በስተምሥ
ራቅ ሐይ ተብሎ በሐገሬው ሰው በሚጠራ
ው ከፍተኛ ተራራ ባጠገቡ ቧሂት የሚባል
በረድ የሚፈላበት ተራራ አለ በሁለ
ቱም ተራሮች መከከል የጻድቃን (የቀ
ዱሳን) አፅም የሚገኝበት ትልቅ ዋሻ ይገ
ኛል በዚሁም ዋሻ የሚገኘው የቅዱሳን
አፅም የኛ ሰዎች የአልተለያየ አፅም ሲሆን
የቀረው ግን የደቀቀና የተለያየ ነው ።

በዚህ ሀገር የሚገኙትም ምእመናን
ለጥምቀት በዓመት በዓመት ታቦት ይዘው
እየወረዱ በዋሻው ውስጥ ቅዳሴ እንዲ
ቀደስና እንዲሁም በመንፈቅ በመንፈቅ
ማዕጠንት እንዲታጠን ያደርጋሉ ሐይ
ማለት ከፍተኛ ተራራ ማለት ነው ፈረ
ንጆች ከፍተኛ ተራራ ሲሉ high Mo -
untain ሐይ ማውንቴን ይላሉ ።

በኒህ በ፫ቱ ተራሮች በኅዳርና በታ
ኅሣሥ ወር በረዱ መንገድ አያስኬድም
በዋሻውም ውስጥ የሚፈላው በረድ
ፀሐይ ሲወጣበት እየቀለጠ ወደ « ውኃ
ነት በሐርዩ በሚለወጥበት ጊዜ የመድፍ
ያህል ይጮሃል የሰማይም ነጐዳ » ይመ
ስላል ከዱር እንስሳትም ወገን ዋሊያዎች
በብዛት የሚገኙት በኒህ ተራሮች ነው
እንጂ በሌላ ቦታ አይገኙም የእንስሳነት
በሕርያቸውም ከፍየል ወገን ሲሆን በጣም
ከፍተኛነት አላቸው ከፍተኛነታቸውም
እንደ ወይፈን ፤ እንደ ጊደር ይሆናል
ቀንዳቸውም ፫ ክንድ ነው በዚያ ሀገር
የሚገኙት ሕዝቦች እኒህን እንስሳት እያ
ደኑ በሥጋቸውና በቈዳቸው ከመጠቀ
ማቸውም በላይ ቀንዳቸውን ዋንጫና
ለሌላም ልዩ ልዩ መሳሪያዎች መያዣና
መጨበጫ እንዲሆኑ እየሸጡ ይጠቀ
ሙባቸዋል የሀገሩ ባላባት የነበሩት ዝነ
ኛው ራስ ገብሬ በዘመናቸው ለመታሰ
ቢያ ያህል ዋንጫ እያሰሩ ለብዙዎች
አድባራት ሰጥተዋል ይኸውም የዋሊያ
ዋንጫ በዘመናቸው ከሠሯቸው
ቤተ ክርስቲያኖች በብዛት ይገኛል
ቤተ ክርስቲያኖቹም ፩ኛ በጊዳ ኢየሱስ
ተብሎ የሚጠራው ደብር ሲሆን ደግሞ
ሁለተኛዋ ደብረ ማርያም ተብላ የምት
ጠራዋ ገዳም ናት ይኸችውም ገዳም
የምትገኘው ከኒህ ከላይ ከተጠቀሱት ተራ
ሮች በምሥራቅ በኩል ነው ቤተ ክር
ስቲያኗም የምትገኘው እንደ ደብረ ዳሞ
በገመድ ላይ ወጥቶ ነው እንጂ በሌላ
በኩል አትገኝም ዙርያዋ ኢልም ያለ
ገደል ነው የጥንት መጻሕፍት በብዛት
ይገኙባታል ። ፫፻ መዝሙረ ዳዊትም
የሚገኘው ከዚችው ገዳም ነው የጎንደር
ጽዮን የእስተርዮ ትክብራለች እጅ ለመ
ንሳት የሚሄዱትን ምእመናን መነኮሳቱ
በክብር ተቀብለው በዚሁ የዋሊያ ዋንጫ
በመጠጥና በመብል ያስተናግዱታቸዋል በሀ
ዋንጫውም ፩ና ፱ ክንድ ይሆናል በሀ
ገሩም ሀብት በብዛት የሚገኘው ንብና
በግ ነው የሚያበቅለውም እህል ገብስ
ነው ከዕፀዋትም ወገን ጅብሩና ኀሳ
እስታ የሚባል እንጨት ነው እንጂ ሌላ
ዕፀዋት አይገኝበትም ።

መ መልአኩ ፈለቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ጸሎት . . .

ከ፪ተኛው ገጽ የዞረ ።

ለመታመዋል ። ሴሎችም ተጽፈው ለመታተም የቀረቡ ብዙ ድርሰቶች ነበሩአቸው ።

አቡነ ፓላዲያን የኮሌጃችን ዲን ሁነው ሦስት ዓመት ሠርተዋል ። የመጀመሪያው ዲን በመሆናቸው ስለ ኮሌጁ ዕድገት ከፍ ያለ ትግል አድርገዋል ። ለጸረሰባቸውም ድካምና ችግር እኛ የዓይን ምስክሮች ነን ።

ብፁዕ አቡነ ፓላዲያን መንፈሳዊው ኮሌጅ በደንብ ተስፋፍቶ መልክም ዕውቀትና ዓላማ ያላቸው ደቀ መዛሙርት የትምህርት ፤ የመንፈሳዊ ተግባር ዝንባሌ የሚገኝበት መዲና ሆኖ ለማየት የጋለ ምኞት ነበራቸው ፤ በንግግራቸውም ላይ ሁልጊዜ መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን ወታደር ለሆነና ለሚሆንም ሰው ሁሉ ፤ ትልቅ ዕውቀት ፤ የፀና ሃይማኖት ፤ እንዲሁም ያወጣኛል ብሎ የሚከተለው ፤ የወደፊት የሥራ ፕሮግራሙን መስተዋት ሆኖ የሚያሳይ የጠነከረ ዓላማ ሊኖረው ያሻል ሲሉ መላልሰው ያስረዱ ነበር ።

አቡነ ፓላዲያን በሥራ የሚአምኑና ለጊዜዋ ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጡ ሰው ነበሩ ። አንድ ተማሪ አንድ ደቂቃ እንኳን ቢሆን በከንቱ እንዲአሳልፍ አይፈቅዱም ነበር ። ስለ ዕድሜም በሚናገሩበት ጊዜ «ብዙ ኖረ የምንለው ሰው ብዙ የሚያስብና ብዙ የሚሠራ ብቻ ነው ። ለህገሩም ሆነ ለወገኖቹ የሚበጅ ሥራ ሳይሠራ ብዙ ዘመን የሚኖር ሁሉ ግን ቦታ ከማጣበብ በቀር ሌላ ጥቅም አይሰጥም ። መኖሩም ከአለመኖሩ ልዩነት የለውም» ሲሉ ያስተምሩ ነበር ።

በኒህ ታላቅ ሰው ድንገተኛ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ልባችን በኀዘን ፍላፃ ተወግቷል ። በአንድ በኩል ግን ለደንበኛ ክርስቲያን ሞቱ ፤ ከሙታን ዓለም ወደ ሕያዋን ዓለም መዛወር እንጂ ወደ ሐቅየ ስነን መሄድ አለመሆኑን ስናስታውስ እንጽናናለን ፤ ደግ በመሥራት በዚህ ዓለም ያለውን የኑሮ ክንትራት ፈጽሞ የሞት ጥላ ያረፈበትን ሁሉ ፤ ከሥጋዊ ዓለም ወደ መንፈሳዊ ዓለም ተዛወረ ፤ ከድካም አረፈ ፤ አንቀላፋ እንጂ ሞተ አንልም ።

ስለዚህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሳቸውን መከነ ዕረፍትን እንዲአወርሳት እንለምነዋለን ፤ እንማለደዋለን ።

# ቤተ ክርስቲያንና

## ቤተ ጸሎት

በአዲስ አበባ ከተማችንም ሆነ በውጪ ፤ ከቤተ ክርስቲያን አጠገብ ቤተ ጸሎት እየተባሉ የሚቋቋሙና ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደውን ሕዝብ ግባና ጸሎት ስማ በማለት የሚያሰናክሉ ሰዎች በብዛት መኖራቸው ሲታወቅ የሰበከው ሕዝብና የሚመለከተው የደብር አለቃ ዝም ብሎ መመልከት ላስተዋለው ሰው አሳፋሪ ነው ።

እያንዳንዳችን ባለንበት ሆነን መከልከል ግዴታ ቢሆንም ቅሉ በተቀዳሚ ሊያስቡና በጥብቅም ሊከራከሩ የሚገባቸው የደብር አለቆች መሆን እንዳለባቸው ማንም የሚፈርደው ነው ።

የኢትዮጵያ ጠ. ቤተ ክህነት በየደብሩ አለቆችን፤ በየጠቅላይ ግዛቱ ሊቃነ ጳጳሳትን በየአውራጃው ኤጲስ ቆጶሳትን መሾሙ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአባቶች ሃይማኖት ጸንቶ እንዲኖርና የኔን ሃይማኖት ተከተል ፤ የኛን ባህል ያዝ እየተባለ ከመዋከብ እንዲድን መሆኑን እናውቀዋለን ።

በየአብያተ ክርስቲያናቱ አቅራቢያ ቤት ተከራይተው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብለው ሰይመው በግራማፎ (በድምፅ ማጉሊያ) ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አትለፋን ፤ ግቡልን እያሉ በመለመን ከትልቁ ሕዝብ ጋር ንትርክ ሲያነሡ ፤ ከሕፃናቱ ጋር በከረሜላ ፤ በብስኩት ፤ በወተት ሲስማሙ የሚኖሩ ሁሉ እስከ መቼ እንደሆነ ጊዜውን ማወቅ አለብን ።

ምንም እንኳ አረማውያንን ለማስተማር ፈቃድ ቢሰጣቸውም ቅሉ በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሌላ ማለት ቤተ ክርስቲያንና ሰበክያን ካሉበት ቦታ ያላመነ አረማዊ እንደሌለ ማንም የሚፈርደው ነው ፤ እውነት ስለ ክርስቶስ ብለው የተነሡ ከሆኑ በክርስቲያኑ ሕዝብ መከከል ገብቶ ሃይማኖትህ እውነተኛ አይደለምና የኛን አዲሱን ሃይማኖት ተከተል እያሉ ባልና ሚስት ፤ አባትና ልጅ ጐሣና ጐሣ ከማለያየትና ከማጣላት ወደ አዳል ወረድ ብለው በቈላ የሚኖረውን ዘላንን ቢያስተምሩ ዋጋ ያገኙ ይሆናል ፤ ቢሆንም እስከዚያው ድረስ በየቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ያሉትን ቤተ ጸሎቶች ለማስወገድና ለማስነሣት የሚመለከታቸው የደብር አለቆች መጀመሪያ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ተነጋግረውበት በሥራ ለመግለጽ መሞከር አለባቸው እያልን እኔና መሰሎቼ ስናስታውሳቸው በትሕትና ነው ።

አጽብሐ ገብረ ጊዮርጊስ ።

# በእህልና

## በውኃ ብቻ ለማደግ አይቻልም ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶችን በወጣቶች ለማስተማር የምታደርገው ጥረት ከግቡ ደርሶ ይኸው ፍሬውን ለመታጨድ ቀርቧል ።

ሕፃናት በእህልና በውኃ ብቻ ለማደግ አይችሉም፤ ከሕፃንነት ወደ ማዕከላዊነት ሊሸጋገሩ የሚችሉት ከእግዚአብሔር በሚሰጣቸው መንፈሳዊ ምግብ ጭምር ነው ። አንድ ሰው ዕገሌ ሽማግሌ ነው ሊያሰኘው የሚችለው የአክሉ መግዘፍና የዕድሜው ርዝመት ብቻ ሳይሆን በአዋቂነቱና በአስታዋይነቱ መሆኑ የተለመደ ነው። በአሁኑ ጊዜም ሕፃናት በጥሩ አስተዳደጋቸውና በትምህርት ተከታታይነታቸው የትልቅነትን ስም ለማግኘት ችለዋል ።

ይኸውም የሆነው በትምህርት ቤቶች መስፋፋትና በአስተማሪዎች ብዛት መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይሆንም ።

ለማስረጃ ያህል እኛ ከ700 በላይ የምንሆን ሕፃናት ከዘመናዊ ትምህርት ጋር የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት አውቀን መገኘታችን ይህ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

በሌላም ትምህርት ቤት የሚገኙት ወንድሞቻችን በዚሁ ይዞታ እንደሚራመዱ ይኸው አሁን ለማየት ችለናል ።

ልጓም የሌለውን ፈረስ ገቶ ለማስቀረት እንደማይቻል በሥጋዊ ትምህርት ላይ መንፈሳዊ ትምህርትን ያላዋሀደ ሰውም ራሱን ከኃጢአት ወስኖ ፤ ገቶ ለማስቀረት አይችልም ።

ስለዚህ እኛም ይህን የግብረ ገብነት ትምህርት እንድንማር ቤተ ክርስቲያን የምታስገድደን ከማንኛውም ስሕተት እንድንርቅላት ነው ።

አሁንም ይህ የተማርነው ትምህርት ብቻ በቂ ይሆነናል ሳንል ሌት ከቀን ተግተን ለመማር እንድንችል የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኛ ጋር ይሁን እያልኩ ንግግሬን ከዚሁ ላይ አቆማለሁ ።

ከመናገሻ ቅ| ጊ| ት| ቤት ቦጋለ ሀብረት

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።

www.ethiopianorthodox.org